# 2024

## አመታዊ ሪፖርት



DC PUBLIC CHARTER SCHOOL BOARD

## ስለ አርቲስቶቹ፡-

የፊት ሽፋን ጥበብ በ**Dameechy Coates**፣ በMary McLeod Bethune  Day Academy PCS የ8ኛ ክፍል ተማሪ

*አክሬሊክስ በወረቀት ላይ*

የኋላ ሽፋን ጥበብ በE.W. የ5ኛ ክፍል ተማሪዎች Stokes PCS

# SY 2022 - 23 ዓመት በግምገማ

**134** የሚንቀሳቀሱ ካምፓሶች 69 የአካባቢ ትምህርት ኤጀንሲዎች (LEAs)

**7,442** ከ9ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የተመዘ ገቡ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች።

**23,962** ከPK3-5 ክፍል የተመ ዘገቡ ተማሪ ዎች

**9,015** ከ6ኛ እስከ 8ኛ ክፍል የተመዘገቡ የመለስተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች።

**48%** በሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከተመዘገቡ ተማሪዎች

**47,566** በ 2023-2024 የትምህርት ዘመን በህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት የተማሩ ተማሪዎች፣ ካለፈው የትምህርት ዘመን የ**2.53%** ጭማሪ

**የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ምዝገባ መረጃ**

የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች በ2023-24 የትምህርት ዘመን **47,566** ተማሪዎችን ወይም **48%** መዝግበዋል። ከታች፣ በህዝብ ቻርተር ትም ህርት ቤት (PCS) የተመዘገቡትን ተማሪዎች መቶኛ በክፍል እና በተማሪ ብዛት የሚያሳይ መረጃ ያገኛሉ፦

- **PK3-PK4** - 13.6%
- **K-5** - 36.9%
- **6-8** - 18.9%
- **9-12** - 15.7%
- **አዋቂ** - 11.7%
- **አማራጭ** - 3.4%

**2022-2023 የአራት-አመት የምረቃ ምጣኔ:- 80%**

የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ከተለምዷዊ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ይልቅ በአብዛኛዎቹ ብዙ ተማሪዎችን ያስመርቃሉ። የሕዝብ ቻርተር ትም ህርት ቤቶች የአራት-ዓመት የምረቃ መጠን 80% ሲሆን ይህም ከ2020-2021 የትምህርት ዘመን ጭማሪ ነው። የአምስት-አመት የተስተካከለ የቡድን ምጣኔ 84.4% ነው።

**የምረቃ ምጣኔዎች በተማሪ ቡድን** *(የአዋቂ ፕሮግራሞችን አያካትትም)*

- 76% ከጥቁር ተማሪዎች
- 84% ከሂስፓኒክ ተማሪዎች
- > 90% ከእስያ ተማሪዎች
- > 95% ከነጭ ተማሪዎች
- 66% ከአካል ጉዳተኛ ተማሪ
- 70% ለአደጋ ከተጋለጡ ተማሪዎች
- 72% ከጀማሪ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪዎች



# ይዘቶች


**የዋና ዳይሬክተር መልእክት** 3

**ASPIRE፣ የእኛ የአካዳሚክ ግምገማ ስርዓት** 4

**የቦርድ አባሎቻችን** 8

**ስትራቴጂያዊ ሮድማፕ** 11

**ምርጥ ትምህርት ቤቶች** 12

የትምህርት ቤቶች ዝርዝር 13

**ዘላቂ አጋርነቶች** 25

**ውጤታማ ድርጅት** 27

**የቦርድ ድርጊቶች** 30

**እኛ ማን እንደሆንን** 33

**የትምህርት ቤት ማሻሻያ ድንጋጌ መስፈርቶች** 36


# ዳራ

በ1996 የተፈጠረው የDC የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ቦርድ (DC PCSB) የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲዎች (LEAs) ተብለው በሚጠሩ 69 ራሳቸውን ችለው በሚተዳደሩ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ለሚመሩ 134 ከተማ አቀፍ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች አካዳሚያዊ እና የፋይናንስ ቁጥጥርን የሚሰጥ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ገለልተኛ የመንግስት ኤጀንሲ ነው።

በዋሽንግተን ዲሲ ውስጥ ብቸኛው የPCS ፈፃሚ እንደመሆናችን መጠን የእኛ ሚና ከትምህርት ዲስትሪክት የተለየ ነው። የ PCS አስተዳደርን አናንቀሳቅስም ወይም አንመራም፣ ያ የእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የባለአደራዎች ቦርድ ሥራ ነው። ይልቁንም፣ መምህራን እና የትምህርት ቤት አመራሮች የተቻላቸውን ስራ ይህም ተማሪዎችን ማስተማር እንዲሰሩ የሚያስችሏቸውን ፖሊሲዎች እና ሁኔታዎችን እንፈጥራለን። ይህ አመታዊ ሪፖርት ከኦገስት 1፣ 2023 እስከ ጁላይ 31፣ 2024 ያለውን ጊዜ ይሸፍናል።

በጁላይ 30፣ 2024 የታተመ ሪፖርት።

**መልእክት ከዋና ዳይሬክተር፣ ዶክተር Michelle Walker-Davis**



የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች በዋሽንግተን ዲሲ ከ20 ዓመታት በላይ ቆይተዋል።
በዚያ ጊዜ ውስጥ፣ የተማሪዎችን እና የቤተሰብን የሚጎለብት ፍላጎት አሟልተዋል።

በኮቪድ ወቅት፣ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ከትምህርትም በላይ በማቅረብ ተደራሽነታቸውን አስፋፍተዋል።
የተማሪዎቻቸውን እና የቤተሰቦቻቸውን አስፈላጊ ፍላጎቶች ለማሟላት፣ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ብዙ ጊዜ የዕለት ተዕለት የተመጣጠነ ምግብ፣ የጤና እንክብካቤ እና የአዕምሮ ጤና ድጋፍ ይሰጣሉ። ለብዙ ማህበረሰቦች እንደ አስፈላጊ ማዕከል ሆነው ቆመው አገልግለዋል።

እንዲሁም ብዙ ትምህርት ቤቶች ከኮቪድ ትምህርት ወስደዋል እና እነዚህን አዳዲስ አቀራረቦች ተግባራዊ እያደረጉ ነው።
ለምሳሌ፣ አንዳንዶች አሁንም የቨርቹዋል ማስተማር እና የበለጠ ተለዋዋጭ መርሃ ግብሮችን ለአስተማሪዎቻቸው ይሰጣሉ።

ትምህርት ቤቶች እነዚህን እና ሌሎች ፈጠራዎችን ብዙ ጊዜ ከዲሲ PCSB ጋር በመተባበር ሞክረዋል። በትምህርት ቤቶች ውስጥ ያለው ሥራ ተቀይሯል፣ የእኛም ሥራ እንዲሁ ተቀይሯል። እና የዲሲ ፒሲኤስቢ እና የትምህርት ቤት መሪዎች ጥምር ስራ የአካዳሚክ ግምገማ ስርዓታችንን እንደገና እንዲመረመር እና እንዲሻሻል አድርጓል፣ እሱም ASPIRE ብለን እንጠራዋለን።

ASPIRE ዓመታዊ የትምህርት ቤት አፈጻጸም መረጃ ጠቋሚ ሪፖርት እና ግምገማ ማለት ነው። በቀላል አነጋገር፣ ASPIRE ማለት ለሁሉም፣ በተለይም በታሪክ ከተገለሉ ማህበረሰቦች ለመጡ ተማሪዎች ምርጥ ትምህርት ቤቶችን ማሳካት ማለት ነው። ASPIRE እያንዳንዱ የዲሲ ተማሪ ጥራት ያለው ትምህርት እንዲያገኝ የDC PCSBን አጠቃላይ እይታ ይደግፋል ይህም ዋጋ እንዳላቸው እንዲሰማቸው እና ለዕድሜ ልክ ትምህርት፣ አርኪ ስራ እና ኢኮኖሚያዊ ደህንነት ያዘጋጃቸዋል። **[ገጽ 5]**። ASPIRE ለተማሪዎች፣ ለትምህርት ቤቶች እና ለትምህርት ጥሩ ነው። ትምህርት ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች ፍትሃዊ ውጤት ማምጣት አለባቸው ብለን በመሠረታዊነት እናምናለን።

የጥራት ፍቃድ መስጠት DC PCSB የስትራቴያዊ ሮድማፕ ቅድሚያ የምንሰጣቸውን ነገሮች እውን ለማድረግ የሚጠቀምበት ቁልፍ ስትራቴጂ ነው። **[ገጽ 11]**። የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት/ፈቃጅ ግንኙነት እምብርት ነው። የሚከተሉትን አምስት መሳሪያዎች በመጠቀም DC PCSB የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶችን በአካዳሚክ ተጠያቂነት፣ በፋይናንስ ትንተና እና በተገዢነት ግምገማ (አስፈላጊ ህጎችን ያካተተ) ይመዝናል፦

1. <u>የቻርተር ግምገማ እና እድሳት ሪፖርቶች</u>፦ አንድ ትምህርት ቤት የቻርተር ግቦቹን እና የአካዳሚክ ስኬት ተስፋዎችን ለማሳካት ያለውን ሂደት ለመገምገም በየአምስት አመቱ የሚደረግ ትንታኔ፣ የትምህርት ቤቱን ቻርተር እና የሚመለከታቸው ህጎችን ማክበር እና የፊስካል አስተዳደር እና ኢኮኖሚያዊ አዋጭነት።**[Page 18]**
2. <u>ጥራት ተኮር የጣቢያ ግምገማዎች (QSR)</u>፦ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶችን የመማሪያ ክፍል አካባቢ እና ትምህርት አጠቃላይ ጥራት ለመገምገም ወቅታዊ ትንታኔዎች። ይህ የምደባ ናሙና ግምገማዎችን ያካትታል፣ ይህም የተማሪ ምደባዎች ለክፍል-አግባብ ከሆኑ ስታንዳርዶች ጋር የተጣጣሙ መሆን አለመሆናቸውን ይገመግማሉ።**[Page 19]**
3. <u>የፋይናንስ ትንተና ሪፖርት</u>፦ የሕዝብ ቻርተር የሚያንቀሳቀስ የእያንዳንዱ ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት የፋይናንስ ዓመታዊ ትንተና ትምህርት ቤት።**[ገጽ 23]**
4. <u>ቀጣይ ክትትል</u>፦ ሁሉም የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች የሚመለከታቸው ህጎችን እንደሚያከብሩ የሚያረጋግጥ አመታዊ ግምገማ። **[ገጽ 23]**
5. <u>ASPIRE</u>፦- የትምህርት ቤት ቁጥጥር ውሳኔዎችን ለማድረግ ጠቃሚ መሳሪያ የሆነው የእኛ የአካዳሚክ ግምገማ ስርዓት።  ASPIRE በደማቅ ቦታዎች ላይ የበለጠ ብርሃን እንድናበራ እና የተማሪን የትምህርት ውጤት ለመጨመር ብዙ የምንሰራው ስራ ሲኖረን ይረዳናል። **[ገጽ 5]**

ይህ አመታዊ ሪፖርት ትምህርት ቤቶች ጥራት ያለው ትምህርት የሚሰጡበትን ሁኔታ ለመፍጠር እና ባለድርሻዎቻችን - ወላጆች/ቤተሰቦች፣ የትምህርት ቤት መሪዎች፣ መምህራን እና የማህበረሰብ መሪዎች - የስራችንን ዝርዝር ውጤት ለማየት ስራችንን እና እድገታችንን የምንገመግምበት ነው።

ከአክብሮት ጋር፣



Michelle J. Walker-Davis, Ed. D
ዋና ዳይሬክተር

# ASPIRE

DC PCSB ትምህርት ቤቶችን ለመገምገም እና የተማሪውን የኮሌጅ እና የስራ ዝግጁነት እድገት በተሻለ ለመረዳት የአካዳሚክ ግምገማ ስርዓቱን ከልሷል።

# የቻርተር ትምህርት ቤት አካዳሚክ ተጠያቂነት

ዲሲ PCSB ትምህርት ቤቶችን ለመምዘን እና የተማሪውን የኮሌጅ እና የስራ ዝግጁነት እድገት በተሻለ ለመረዳት የአካዳሚክ ግምገማ ስርዓቱን ከልሷል። የአካዳሚክ ግምገማ ስርዓቱ አመታዊ የትምህርት ቤት አፈፃፀም መረጃ ጠቋሚ ሪፖርት እና ግምገማ ወይም (ASPIRE) እየተባለ የሚጠራ ሲሆን ከመላ ሀገሪቱ የባለድርሻ አካላት አስተያየት፣ ጥናትና ምርምር እና የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት አካዳሚክ ተጠያቂነት ላይ የተገኙ ምርጥ ተሞክሮዎችን ያካትታል።

የተማሪዎችን ታይነት ከአጋጣሚው የበለጠ ለማሳደግ የአካዳሚክ መሳሪያ ተዘጋጅቷል።  ASPIRE አምስት ማዕቀፎች አሉት እና ዘር እና ጎሳን ጨምሮ የተከፋፈሉ መረጃዎችን ሪፖርት ያደርጋል። ወደ አምስት ደረጃዎች በመሸጋገር፣ ከአፈጻጸም የሚጠበቁትን በማሳደግ እና ለዕድገት የበለጠ ትኩረት በመስጠት የትምህርት ቤት አፈጻጸም ደረጃዎችን ያሰፋል። የሁሉንም የዲሲ ተማሪዎች ልምድ ለማሻሻል ይህ በጣም አስፈላጊ ነው።




DC PCSB ለተጠያቂነት ትልቅ ቦታ የሚሰጥ ከፍተኛ ጥራት ያለው ፈቃጅ በመሆን ረጅም ታሪክ አለው። ASPIRE ብዙ የቻርተር ፈቃጆች ያላደረጉትን ነገር ለማድረግ ያለመ ነው። DC PCSB ቦርዱ በጣም አስፈላጊ ናቸው ብሎ ባመነበት አካባቢ ያሉ ትምህርት ቤቶችን የሚገመግም የአካዳሚያዊ ተጠያቂነት መሣሪያ አዘጋጅቷል።

ይህ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

- ተማሪዎች እንዲያድጉ ማገዝ፣
- ተማሪዎችን ለኮሌጅ እና ለስራ ስኬት ማዘጋጀት፣ እና
- ሁሉንም ተማሪዎች የሚደግፍ የትምህርት አካባቢ መገንባት።

ASPIRE ለተማሪዎች፣ ለትምህርት ቤቶች እና ለትምህርት ጥሩ ነው። እዚህ ለመድረስ ብዙ ርቀት ተኪዷል - ያለውን ስርዓት ለመከለስ ከሶስት አመታት በላይ ፈጅቷል።

ASPIRE ከትምህርት ቤት መሪዎች፣ ቤተሰቦች፣ የትምህርት ቤት ቦርድ አባላት፣ ባለሙያዎች፣ እና ሌሎች በርካታ ሰዎች በተቀበለው ግብአት ምክንያት ጠንካራ ስርዓት ነው። በገጽ 27 ላይ የበለጠ ያንብቡ።

# ከሌሎች ግንዛቤን መፈለግ፣ ሁሉንም ድምፆች በሂደታችን ውስጥ ማሳተፍ

**2021**

| ማርች - ኦውገስት | ኤፕሪል | ሜይ |
| --- | --- | --- |
| **ከአትላንቲክ መካከለኛው ክልላዊ የትምህርት ላቦራቶሪ** (REL) ጋር አጋርነት | **የአነስተኛ ቡድን ማዳመጥ** ከLEA ጋር (26) | **የማህበረሰብ ዳሰሳ** 114 ምላሽ ሰጪዎች 78% ወላጆች/አሳዳጊዎች 11% የማህበረሰብ አባላት |

| ጁን - ኦክቶበር | ኦክቶበር - ዲሴምበር |
| --- | --- |
| **ከብሔራዊ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ተቋማዊ A-CAME** ጋር ያለ አጋርነት | **PK -12 የምክር ክሮፕ** እና **AE የምክር ክሮፕ** ስብሰባዎች (6) |

**2022**

| ጃኑዋሪ - ማርች | ሴፕቴምበር - ዲሴምበር | ኦክቶበር - ዲሴምበር |
| --- | --- | --- |
| **PK -12 የምክር ክሮፕ** እና **AE የምክር ክሮፕ** ስብሰባዎች (6) | **የተጠያቂነት ግብረ ኃይል** ስብሰባዎች (6) | ከ **REL** ጋር አጋርነት |

**2023**

| ጃኑዋሪ - ኤፕሪል | ጃኑዋሪ - ጁን | ኤፕሪል | ኤፕሪል - ጁን |
| --- | --- | --- | --- |
| **የተጠያቂነት ግብረ ኃይል** ስብሰባዎች (10) | ከ **REL** ጋር አጋርነት | የተጠያቂነት አቀራረብ ለወላጅ እና **የቀድሞ ተማሪዎች አመራር ምክር ቤት** | የDC PCSB **ዋና ዳይሬክተር ከትምህርት ቤት መሪዎች** ጋር ስብሰባዎች (12) |

| ሜይ | ጁን | ጁላይ |
| --- | --- | --- |
| የቻርተር ኮልስ ፖሊሲ (ክፍል 1) **የቢሮ ሰዓቶች** | **የተጠያቂነት ማዕቀፍ** የህዝብ ውይይት | • **የተጠያቂነት ማዕቀፍ** የህዝብ ውይይት ከ **NACSA** እና **REL**<br>• ቦርድ የቻርተር **ኮልስ ፖሊሲን ያፀድቃል (ክፍል 1)** |

| ኦክቶበር | ዲሴምበር |
| --- | --- |
| የተሻሻለ የተጠያቂነት **ትምህርት ክፍለ ጊዜ (8)** | • **የDC ቻርተር አሊያንስ** የDC PCSB ሰራተኞችን እና የትምህርት ቤቱን መሪ ክፍለ ጊዜ ያስተናግዳል<br>• **የብሔራዊ ቻርተር ትብብር** የDC PCSB ሰራተኞችን እና የቀለም መሪዎችን የትምህርት ክፍለጊዜ ያስተናግዳል<br>• በDC PCSB የቦርድ ስብሰባ ላይ **ከOSSE** ጋር የተጠያቂነት ውይይት<br>• **ባለሙያ ገምጋሚዎች** (6) በASPIRE Tech Guide ላይ ምጋቤምላሽ ይሰጣሉ |

**2024**

**ጃኑዋሪ**

ASPIRE Tech Guide ረቂቅ ለ"መጀመሪያ እይታ" **ለትምህርት ቤት መሪዎች ተለቋል**

**ጃኑዋሪ - ፌብሩዋሪ**

- ASPIRE Tech Guide **የቢሮ ሰአታት** ለትምህርት ቤት መሪዎች
- የቻርተር ግቦች ፖሊሲ የትምህርት ክፍለ ጊዜዎች **ለትምህርት ቤት መሪዎች**

**ፌብሩዋሪ**

- የASPIRE ፖሊሲ እና Technical Guide ለህዝብ **አስተያየት ተከፍቷል**
- የቻርተር ግቦች ፖሊሲ ለህዝብ **አስተያየት ተከፍቷል**

**ማርች**

- የቻርተር ኮልስ ፖሊሲ **የቢሮ ሰዓቶች** ለትምህርት ቤት መሪዎች
- HS የተጠያቂነት **ግብረ ኃይል ስብሰባ**
- ASPIRE Tech Guide **የህዝብ ችሎት #1**

**ኤፕሪል**

- ASPIRE Tech Guide **የህዝብ ችሎት #2 እና #3**
- የቻርተር ኮልስ ፖሊሲ **የህዝብ ችሎት**
- የ **ASPIRE ግንኙነት** ባለሁለት ሳምንት ኤሌክትሮኒክ-ዜና መጀመር

**ሜይ**

- AE ማዕቀፍ የንግድ **ሕጎች ከ AE ትምህርት ቤቶች ጋር ተጋርተዋል**
- በ**PALC** ስብሰባ ላይ የASPIRE አቀራረብ
- **ቀይ መስመር ያለው ASPIRE Tech Guide** ከትምህርት ቤቶች ጋር ተጋርቷል

**ጁን**

**ለትምህርት ቤት መሪዎች** ASPIRE የስርዓት ትምህርት ክፍለ ጊዜዎች

የ ASPIRE ፖሊሲ እና የቴክኒክ መመሪያ እና የቻርተር ግቦች ፖሊሲ የASPIRE ስርዓትን የሚመሰረቱ የአጋር ፖሊሲዎች ናቸው። የASPIRE ፖሊሲ እና የቴክኒክ መመሪያ የDC PCSB ትምህርት ቤቶችን በየዓመቱ ለመገምገም ያለውን አካሄድ በዝርዝር ይገልጻል። ተጓዳኝ የቻርተር ግቦች ፖሊሲ የግምገማ መሣሪያውን እንደ ቻርተር ግምገማዎች እና እድሳት ግቦች እና ልዩ የቻርተር ግቦችን የማውጣት መስፈርት አድርጎ ለመውሰድ የሚያስችል ዘዴን ያስቀምጣል።

የእኛን ነጭ ወረቀት ያንብቡ እና ስለ እያንዳንዱ ፖሊሲ የበለጠ ይወቁ፦
https://dcpcsb.org/aspire

**አጋሮች ስለ ASPIRE ምን እያሉ ነው**

DC PCSB የአካዳሚክ ግምገማ ስርዓታችንን ASPIRE የማዘጋጀት ጥረታችንን ያገዙን አጋሮቻችንን በጣም ያመሰግናል። የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ብሔራዊ ትብብር ስለ ASPIRE የተናገረው ይኸውና፡-

> *"የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች ብሔራዊ ትብብር የዲሲ ብቸኛ ቻርተር ባለስልጣን የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶችን አፈጻጸም በጥብቅ እንዲገመግም እና እንዲደግፍ የሚያስችል ፈር ቀዳጅ የአካዳሚክ ተጠያቂነት ስርዓት የሆነው ASPIREን ለመፍጠር እና ለማስጀመር ለሚያደርጉት ስራ DC PCSBን ያመሰግናል።"*

የቻርተር ትምህርት ቤት ፈቃጆች ብሔራዊ ማህበር (NACSA) ድጋፋቸውን አሰምተዋል፡-

> *"NACSA DC PCSB በዲሲ ላሉ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የበለጠ ጠንካራ ትምህርት ቤቶችን ለማፍራት በተዘጋጀው ASPIRE ስርዓት በኩል የተጠያቂነት አካሄዳቸውን ያደንቃል።"*



**Lea Crusey**
ሊቀመንበር | ዋርድ 6



**Jim Sandman**
ምክትል ሊቀመንበር | ዋርድ 6



**Shantelle Wright**
የግምጃቤት ሀላፊ | ዋርድ 8



**Shukurat Adamoh-Faniyan**
ጸሃፊ | ዋርድ 6



**Nick Rodriguez**
አባል | ዋርድ 6



**Carisa Stanley Beatty**
አባል | ዋርድ 8

# ለዘር፣ ፍትሃዊነት፣ ብዝሀነት እና ለአካታችነት ያለን ቃል ኪዳን

በትምህርት ቤት ማሻሻያ ድንጋጌ እና የዘር፣ ፍትሃዊነት፣ ብዝሃነት እና የአካታችነት ስራ ላይ የተመሰረተ፣ DC PCSB ለተልዕኮው አገልግሎት ጊዜ ወስዶ ለማንፀባረቅ፣ ለማዳመጥ እና ለሌላው ቦታ ለመያዝ ቃል ገብቷል። ቦርዱ ይህን የመፍቀድ ስራ ወደፊት እንዲራመድ በሚመሩ የሚከተሉት እምነቶች እና ቃል ኪዳኖች አንድ ነው፦

- በአገራችን የግለሰቦች፣ የተቋማት እና የስርአት ዘረኝነት መስፋፋቱን መገንዘብ።
- ዘረኝነት እና ኢፍትሃዊነት በሕዝብ ትምህርት ላይ የሚያሳድረውን የጋራ ተጽእኖ እና እነዚህን ጉዳቶች ለማስቀጠል ያለንን ሚና ለመረዳት መፈለግ።
- ጥሩ ትምህርት ቤት ፍትሃዊ ነው ብለን ማመን።
- እንደ የዲሲ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ባለስልጣን በተማሪዎች ላይ የዘረኝነት እና ኢፍትሃዊነት ተጽእኖ ለማስወገድ መስራት።
- ፖሊሲዎቻችንን፣ ተግባሮቻችንን፣ ምክሮቻችንን እና ባህሪያችንን ለማሳወቅ ስለራሳችን፣ ስራችን እና ከተማችን ያለማቋረጥ ለመማር ቃል መግባት።
- ሁሉንም ድምጽ በውሳኔ አሰጣጥ ሂደታችን ውስጥ በጥልቀት እና በቋሚነት ማሳተፍ እናም ሰዎች በቦርዱ ስራ ላይ ያላቸውን የግል ልምዳቸው እና አመለካከታቸውን ሲያካፍሉ ሊመጣ የሚችለውን አለመግባባት መቀበል።



# ዋና እሴቶቻችን

ዋና እሴቶች ሁሉንም ነገር ይመራሉ፣ እና በእውነቱ የዚህ ድርጅት ማዕከል ናቸው። የሚከተሉትን በተመለከተ ልዩ የሆነ ባህል እንድናዳብር ይረዱናል፡-

**ቁርጠኝነት** – ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን ለማገልገል እና ለሁሉም ውጤቶችን ለማሻሻል በትብብር ለመስራት ቁርጠኝነት አለ።

**እንክብካቤ** - ሁሉም ሰው በሙያዊ እና በግል በጓደኛዊ እና አዝናኝ አካባቢ ይደገፋል

**ልህቀት** - ከፍተኛ ጥራት ያለው ሥራ የሚመረተው የሕዝብ ትምህርት ቤቶችን ለማሻሻል እና በመረጃ፣ በፍትሃዊነት፣ በመልካም አስተሳሰብ እና በቦርዱ ፖሊሲዎች በማክበር ውሳኔዎች ላይ የተመሰረተ ነው።

**ንጹህነት** - የDC PCSB እና የህዝብ ቻርተር ሴክተር ታማኝነት የሚስፋፋው ስነምግባራዊ፣ ግልጽ እና ታማኝ በሆኑ ቃላት እና ድርጊቶች ነው።

**ተነሳሽነት** – እንቅፋት ሳይሆን እድሎች ላይ እናተኩራለን፣ በንቃት አዳዲስ መፍትሄዎችን በመፍጠር እና ውጤትን ለማግኘት እንቅፋቶችን ማስወገድ።

**ጽብረቃ** - ቀጣይነት ያለው ትምህርት እና መሻሻል ላይ ለመሳተፍ ግብረመልስ በደስታ ይቀበላል፣ እና ቦርዱ በቀጣይ ስራ የተማረውን ተግባራዊ ለማድረግ ይጥራል።



# በስትራቴጂ ፍኖተ ካርታ ላይ እድገት




የቦርዱ ሰሜናዊ ኮከብ ሆኖ የቀጠለው የስትራቴጂ ፍኖተ ካርታው የቦርዱን ምኞቶች እና ጥረቶች በሶስት ቅድሚያ በሚሰጣቸው ጉዳዮች ይመራል፦ ምርጥ ትምህርት ቤቶች፣ ዘላቂ አጋርነት እና ውጤታማ ድርጅት። ይህ በምናደርጋቸው ነገሮች ሁሉ ቅድሚያ ፍትሃዊነትን፣ ጥራትን እና ምርጫን ለማስቀጠል የማይናወጥ ቁርጠኝነትን ያሳያል።

ወላጆች/ቤተሰቦችን፣ የትምህርት አጋሮችን፣ የተመረጡ መሪዎችን እና ብዙ ሌሎችን በማሳተፍ ፣ DC PCSB በመጀመሪያ እና በዋናነት በተማሪዎች ላይ ማተኮር ይቀጥላል። የእኛ ስራ መምህራን እና የትምህርት ቤት መሪዎች ተማሪዎችን እንዲያስተምሩ የሚያስችላቸውን ፖሊሲዎች እና ሁኔታዎችን ይፈጥራል። የሶስት አመት ግቦች እና ግስጋሴዎችን ለመለካት መለኪያዎች ለሦስቱ ስትራቴጂያዊ ቅድሚያዎች ተቀምጠዋል። ከ44ቱ የስትራቴጂ ፍኖተ ካርታ መለኪያዎች 84 በመቶው በዚህ አመት ሙሉ በሙሉ ተሟልተዋል።

መለኪያዎቹ እንደተዘጉ፣ ቦርዱ በስትራቴጂ ፍኖተ ካርታው በሚቀጥሉት ሶስት ዓመታት በንቃት እያሰላሰለ እና እያቀደ ነው። በተደራጀው መሠረት ላይ በመገንባት፣ እነዚህ ስትራቴጂያዊ ቅድሚያዎች ለሴክተሩ ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት የቦርዱን ድርጅታዊ ዓላማዎች መሠረት በማድረግ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

## ስትራቴጂያዊ ቅድሚያዎቹ

### ምርጥ ትምህርት ቤቶች

የ DC PCSB ውሳኔ አሰጣጥ ለከተማ አቀፍ ፍላጎት ምላሽ መስጠቱን እና ለሁሉም የዲሲ ተማሪዎች በተለይም በታሪክ የተገለሉ ቡድኖች ውስጥ ላሉ የተሻሻሉ ውጤቶችን እንደሚያመጣ ያረጋግጡ።



### ዘላቂ አጋርነቶች

ስለ ስራችን የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር፣ ግብረ መልስ ለመጠየቅ እና በዲሲ ዙሪያ አዳዲስ አጋርነቶችን ለመፍጠር በቤተሰብ፣ በትምህርት ቤት ማህበረሰቦች እና በነዋሪዎች መካከል የሚደረገውን ውይይት ማጠናከር።

### ውጤታማ ድርጅት

DC PCSB በዲሲ የተማሪ ስኬት ሁኔታዎችን እንዲፈጥር ለማድረግ ውስጣዊ መዋቅራችንን፣ ሂደቶቻችንን እና ባህላችንን ከስትራቴጂያዊ እቅዳችን ጋር እንዲጣጣሙ ማድረግ።

https://dcpcsb.org/strategic-roadmap ላይ የበለጠ ይወቁ።

# ምርጥ ትምህርት ቤቶች

የ DC PCSB ውሳኔ አሰጣጥ ለከተማ አቀፍ ፍላጎት ምላሽ መስጠቱን እና ለሁሉም የዲሲ ተማሪዎች በተለይም በታሪክ የተገለሉ ቡድኖች ውስጥ ላሉ የተሻሻሉ ውጤቶችን እንደሚያመጣ ማረጋገጥ።

## ዲሲ የሕዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች

| የትምህርት ቤት ስም | WARD | የፕሮግራም አይነት | 2023 – 24 አገልግሎት ያገኙ የክፍል ደረጃዎች | 2023 - 24 ኦዲት የተደረገ ምዝገባ |
|---|---|---|---|---|
| Academy of Hope Adult PCS | 5, 8 | የጽሁፍና ንባብ እውቀት፣ GED ዝግጅት፣ የኮምፒዩተር ችሎታ፣ መንታ ምዝገባ፣ ቀንና ማታ | አዋቂ | 840 |
| የስኬት መሰናዶ PCS | 8 | መሪነትን ማሳደግ | PK3 - 5 | 323 |
| AppleTree PCS - Columbia Heights | 1 | የልጅነት እድሜ | PK3 - PK4 | 98 |
| AppleTree PCS - Douglas Knoll | 8 | የልጅነት እድሜ | PK3 - PK4 | 51 |
| AppleTree PCS - Lincoln Park | 6 | የልጅነት እድሜ | PK3 - PK4 | 59 |
| AppleTree PCS - Oklahoma Avenue | 7 | የልጅነት እድሜ | PK3 - PK4 | 160 |
| AppleTree PCS - Parklands | 8 | የልጅነት እድሜ | PK3 - PK4 | 99 |
| AppleTree PCS - Southwest | 6 | የልጅነት እድሜ | PK3 - PK4 | 84 |
| AppleTree PCS - Spring Valley | 3 | የልጅነት እድሜ | PK3 - PK4 | 101 |
| BASIS DC PCS | 2 | Liberal Arts | 5 - 12 | 690 |
| Breakthrough PCS | 4 | Montessori | PK3 - 5 | 369 |
| Bridges PCS | 5 | ከልጅነት እድሜ እስከ አንደኛ ደረጃ ትምህርት፤ የልዩ ትምህርት ትኩረት | PK3 - 5 | 365 |
| Briya PCS | 1,4 & 5 | የሁለት-ትውልድ ፕሮግራም፤ እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ፤ የህጻን እድገት ተባባሪ፤ የህክምና እገዛ | PK3 - PK4 እና አዋቂ | 763 |
| Capital City PCS - HS | 4 | የጥበብ ውህደት፣ ፕሮጀክት ተኮር መማር | 9 - 12 | 350 |
| Capital City PCS - LS | 4 | የጥበብ ውህደት፣ ፕሮጀክት ተኮር መማር | PK3 - 4 | 326 |
| Capital City PCS - MS | 4 | የጥበብ ውህደት፣ ፕሮጀክት ተኮር መማር | 5 - 8 | 336 |
| Capital Village PCS | 5 | የጉዞ ትምህርት፣ አነስተኛ ትምህርት ቤት፣ እና ለግል የተበጀ መማር | 5 - 8 | 103 |
| Carlos Rosario PCS | 1, 5 | የመጻፍ እና ማንበብ እውቀት፤ እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ፤ የኮምፒውተር ክሂሎች፤ የምግብ ጥበብ፣ የነርስ እርዳታ፣ የGED እና የዜግነት ዝግጅት | አዋቂ | 2,110 |
| Cedar Tree PCS | 8 | የልጅነት እድሜ | PK3 - 2 | 428 |
| Center City PCS - Brightwood | 4 | Liberal Arts; Humanities | PK3 - 8 | 261 |
| Center City PCS - Capitol Hill | 7 | Liberal Arts; Humanities | PK3 - 8 | 215 |
| Center City PCS - Congress Heights | 8 | Liberal Arts; Humanities | PK3 - 8 | 243 |
| Center City PCS - NoMa | 5 | Liberal Arts; Humanities | PK3 - 8 | 200 |
| Center City PCS - Petworth | 4 | Liberal Arts; Humanities | PK3 - 8 | 242 |
| Center City PCS - Shaw | 2 | Liberal Arts; Humanities | PK4 - 8 | 199 |
| Cesar Chavez PCS | 7 | የህዝብ ፖሊሲ | 6 - 12 | 399 |
| የማህበረሰብ ኮሌጅ መሰናዶ PCS | 8 | የ HVAC ስልጠና፤ የብሄራዊ ደንበኛ አገልግሎት፤ የኮምዩተር ክሂሎች፤ የ CompTIA እገዛ ዴስክ፤ Microsoft Office Suite; ድርብ የኮሌጅ ምዝገባ | አዋቂ | 618 |

## የዲሲ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች *(የቀጠለ)*

| የትምህርት ቤት ስም | WARD | የፕሮግራም አይነት | 2023 – 24 አገልግሎት ያገኙ የክፍል ደረጃዎች | 2023 - 24 ኦዲት የተደረገ ምዝገባ |
|---|---|---|---|---|
| Creative Minds PCS | 5 | ዓለም አቀፋዊ ትምህርት፣ አካታችነት፣ የጥበብ ትምህርት/ ውህደት | PK3 - 8 | 581 |
| DC Bilingual PCS | 4 | ድርብ ቋንቋ፣ የጥበብ ውህደት፣ ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና፣ ሒሳብ (STEM) ተኮር | PK3 - 5 | 579 |
| DC Prep PCS - Anacostia ES | 8 | በይነዲሲፕሊናዊ ስርዓተ ትምህርት | PK3 - 3 | 423 |
| DC Prep PCS - Anacostia MS | 8 | በይነዲሲፕሊናዊ ስርዓተ ትምህርት | 3 - 7 | 265 |
| DC Prep PCS - Benning ES | 7 | በይነዲሲፕሊናዊ ስርዓተ ትምህርት | PK3 - 3 | 425 |
| DC Prep PCS - Benning MS | 7 | በይነዲሲፕሊናዊ ስርዓተ ትምህርት | 4 - 8 | 311 |
| DC Prep PCS - Edgewood ኢኤስ | 5 | በይነዲሲፕሊናዊ ስርዓተ ትምህርት | PK3 - 3 | 420 |
| DC Prep PCS - Edgewood MS | 5 | በይነዲሲፕሊናዊ ስርዓተ ትምህርት | 4 - 8 | 300 |
| DC Scholars PCS | 7 | በይነዲሲፕሊናዊ ስርዓተ ትምህርት | PK3 - 8 | 491 |
| DC Wildflower PCS – The Riverseed School | 7 | Montessori | PK3 - 8 | 28 |
| Digital Pioneers Academy PCS - Capitol Hill | 6 | የኮሚፒዩተር ሳይንስ፣ የተለያዩ ከትምህርት ውጪ የሚገኙ ተሞክሮዎች | 9 - 11 | 287 |
| Digital Pioneers Academy PCS - Johenning | 8 | የኮሚፒዩተር ሳይንስ፣ የተለያዩ ከትምህርት ውጪ የሚገኙ ተሞክሮዎች | 6 - 8 | 312 |
| የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤት | 4 | ጥልቅ የቋንቋ ጥናት፣ ዓለም አቀፍ ባካሉሬት ስርዓተ ትምህርት | 6 - 12 | 1,619 |
| E.L. Haynes PCS - ES | 4 | ተሞክሯዊ መማር | PK3 - 5 | 357 |
| E.L. Haynes PCS - MS | 1 | ተሞክሯዊ መማር | 5 - 8 | 377 |
| E.L. Haynes PCS - HS | 4 | ተሞክሯዊ መማር | 9 - 12 | 439 |
| Eagle PCS - Capitol Riverfront | 6 | የጥበብ ውህደት | PK3 - 3 | 123 |
| Eagle PCS - Congress Heights | 8 | ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና፣ ሒሳብ (STEM) ተኮር | PK3 - 3 | 269 |
| Early Childhood PCS | 8 | የልጅነት እድሜ | PK3 - 3 | 247 |
| EW Stokes PCS - Brookland | 5 | ድርብ ቋንቋ | PK3 - 5 | 351 |
| EW Stokes PCS - East End | 7 | ድርብ ቋንቋ | PK3 - 5 | 342 |
| Friendship PCS - Armstrong Elementary | 5 | Reggio Emilia-Inspired Learning Center | PK3 - 3 | 245 |
| Friendship PCS - Armstrong Middle | 5 | የጥበብ ውህደት | 4 - 8 | 198 |
| Friendship PCS - Blow Pierce Elementary | 7 | የኮሌጅ መሰናዶ ትምህርት ቤት | PK3 - 3 | 273 |
| Friendship PCS - Blow Pierce Middle | 7 | የኮሌጅ መሰናዶ ትምህርት ቤት | 4 - 8 | 237 |
| Friendship PCS - Chamberlain Elementary | 6 | በተማሪ ስኬት ዝና ያተረፉ | PK3 - 3 | 274 |
| Friendship PCS - Chamberlain Middle | 6 | በተማሪ ስኬት ዝና ያተረፉ | 4 - 8 | 303 |
| Friendship PCS - Collegiate | 7 | የኮሌጅ መጀመሪያ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 9 - 12 | 715 |
| Friendship PCS - Ideal Elementary | 4 | Reggio Emilia-Inspired Learning Center | PK3 - 3 | 218 |
| Friendship PCS - Ideal Middle | 4 | የተራዘመ ቀን | 4 - 8 | 172 |

## የዲሲ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች *(የቀጠለ)*

| የትምህርት ቤት ስም | WARD | የፕሮግራም አይነት | 2023 – 24 አገልግሎት ያገኙ የክፍል ደረጃዎች | 2023 - 24 ኦዲት የተደረገ ምዝገባ |
|---|---|---|---|---|
| Friendship PCS - የመስመር ላይ | 4 | ቨርቹዋል ትምህርት ቤት | K - 8 | 397 |
| Friendship PCS - Southeast Elementary | 8 | Every Child Ready Instructional Approach | PK3 - 3 | 368 |
| Friendship PCS - Southeast Middle | 8 | Every Child Ready Instructional Approach | 4 - 8 | 326 |
| Friendship PCS - ቴክኖሎጂ | 8 | ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና፣ ሒሳብ (STEM) ተኮር | 9 - 12 | 327 |
| Friendship PCS - Woodridge አንደኛ ደረጃ | 5 | International Baccalaureate | PK3 - 3 | 244 |
| Friendship PCS - Woodridge መለስተኛ | 5 | አለም አቀፍ ባካሎሬት | 4 - 8 | 214 |
| Girls Global PCS | 2 | አንድ ጾታ፣ አለም አቀፍ ባካሎሬት፣ ቢዝነስ እና ምህንድስና | 9 - 12 | 210 |
| Global Citizens PCS | 7 | ድርብ ቋንቋ/ጥልቅ ትምህርት፣ የተራዘመ ቀን፣ የታደሰ ፍትህ ፕሮግራም | PK3 - 1 | 161 |
| Goodwill Excel PCS | 2, 6 | የትራንስፖርት አገዛ ፣ የሕፃናት እንክብካቤና ተለዋዋጭ የትምህርት የጊዜ ሰሌዳዎች | አዋቂ | 441 |
| Harmony PCS | 5 | ሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ፣ ምህንድስና፣ እና ሒሳብ (STEM) ተኮር | PK3 - 5 | 178 |
| Hope Community PCS - Tolson | 5 | የጉዞ ትምህርት (ጥበብ፣ ቴክኖሎጂ፣ የሳይንስ ምርምር እና ሙዚቃ) | PK3 - 8 | 227 |
| Howard University Middle PCS | 1 | ሒሳብና ሳይንስ ተኮር | 6 - 8 | 253 |
| I Dream PCS | 7 | ባለብዙ-ዕድሜ ቡድኖች፣ የህልም ጊዜ፣ ብጁ የመማሪያ እቅዶች እና ማህበራዊ-ስሜታዊ መማር | PK3 - 4 | 84 |
| IDEA PCS | 7 | አመራር፣ ኮንስትራክሽን፣ እና ዲዛይን ተኮር፤ የኮሌጅ ድርብ-ምዝገባ | 9 - 12 | 309 |
| Ingenuity Prep PCS | 8 | ሕዝባዊ መሪነት፣ ቅይጥ መማር፣ የልጅነት እድሜ | PK3 - 8 | 792 |
| Inspired Teaching PCS | 5 | ጥያቄ ተኮር፣ ሙሉ የህፃናት፣ እና የማህበራዊ ፍትህ አትኩሮት | PK3 - 8 | 522 |
| Kingsman PCS | 6 | ፕሮጀክት-ላይ የተመሰረተ፤ ግላዊነት የተላበሰ ትምህርት | አማራጭ | 326 |
| KIPP DC - AIM PCS | 8 | የሃይ ስኩል መሰናዶ ስርአተ-ትምህርት፤ የአመራር እና ስብእና ግንባታ | 5 - 8 | 435 |
| KIPP DC - ጥበብ እና ቴክ PCS | 7 | ጨዋታ ተኮር የቀለም ትምህርትና የማህበረሰብ ስሜታዊ ስርዓተ ትምህርት | PK3 - 8 | 270 |
| KIPP DC - College PCS | 5 | ዓለም አቀፋዊ ዝግጁነት ላይ ያተኮረ ስርዓተ ትምህርት፤ የስራ መስክ እና የኮሌጅ ስልጠና፤ የላቀ ምደባ ትምህርቶች፤ የፍሬሽማን አካዳሚዎች | 9 - 12 | 696 |
| KIPP DC - Connect PCS | 5 | ጨዋታ ተኮር የቀለም ትምህርትና የማህበረሰብ ስሜታዊ ስርዓተ ትምህርት | PK3 - 8 | 270 |
| KIPP DC - Discover PCS | 8 | ጨዋታ ተኮር የቀለም ትምህርትና የማህበረሰብ ስሜታዊ ስርዓተ ትምህርት | PK3 - 8 | 319 |
| KIPP DC - Grow PCS | 2 | ጨዋታ ተኮር የቀለም ትምህርትና የማህበረሰብ ስሜታዊ ስርዓተ ትምህርት | PK3 - 8 | 236 |
| KIPP DC - Heights PCS | 8 | ጠንካራ አካዳምያዊ ስርአተ-ትምህርት፤ የስብእና እና ሙሉ-ህጻንነት አካሄድ | 1 - 4 | 458 |
| KIPP DC - Honor PCS | 8 | የተዋሃደ መማር | 5 - 8 | 334 |
| KIPP DC - Inspire PCS | 8 | የተዋሃደ መማር | 1 - 4 | 237 |

## የዲሲ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች *(የቀጠለ)*

| የትምህርት ቤት ስም | WARD | የፕሮግራም አይነት | 2023 – 24 አገልግሎት ያገኙ የክፍል ደረጃዎች | 2023 - 24 ኦዲት የተደረገ ምዝገባ |
|---|---|---|---|---|
| KIPP DC - KEY PCS | 7 | የሃይ ስኩል መሰናዶ ስርአተ-ትምህርት፤ የአመራር እና ስብእና ግንባታ | 5 - 8 | 409 |
| KIPP DC - Lead PCS | 2 | ጠንካራ አካዳምያዊ ስርአተ-ትምህርት፤ የስብእና እና ሙሉ-ህጻንነት አካሄድ | 1 - 4 | 370 |
| KIPP DC - LEAP PCS | 7 | ጨዋታ ተኮር የቀለም ትምህርትና የማህበረሰብ ስሜታዊ ስርዓተ ትምህርት | PK3 - PK4 | 226 |
| KIPP DC - Northeast PCS | 5 | የሃይ ስኩል መሰናዶ ስርአተ-ትምህርት፤ የአመራር እና ስብእና ግንባታ | 5 - 8 | 355 |
| KIPP DC - Pride PCS | 8 | የተዋሃደ መማር | PK3 - 8 | 167 |
| KIPP DC - Promise PCS | 7 | ጠንካራ አካዳምያዊ ስርአተ-ትምህርት፤ የስብእና እና ሙሉ-ህጻንነት አካሄድ | K - 4 | 621 |
| KIPP DC - Quest PCS | 7 | ጠንካራ አካዳምያዊ ስርአተ-ትምህርት፤ የስብእና እና ሙሉ-ህጻንነት አካሄድ | 1 - 4 | 390 |
| KIPP DC - Spring PCS | 5 | ጠንካራ አካዳምያዊ ስርአተ-ትምህርት፤ የስብእና እና ሙሉ-ህጻንነት አካሄድ | 1 - 4 | 376 |
| KIPP DC - Valor PCS | 7 | የሃይ ስኩል መሰናዶ ስርአተ-ትምህርት፤ የአመራር እና ስብእና ግንባታ | 5 - 8 | 336 |
| KIPP DC - WILL PCS | 2 | የሃይ ስኩል መሰናዶ ስርአተ-ትምህርት፤ የአመራር እና ስብእና ግንባታ | 5 - 8 | 323 |
| KIPP DC PCS - Legacy PCS | 8 | የተቀናጀ መማር፣ የድርብ ኮሌጅ ምዝገባ፣ የላቀ ምደባ | 9 - 12 | 495 |
| LAMB PCS | 4,5 | ሞንቴሶሪ፣ ጥልቅ የቋንቋ ጥናት | PK3 - 5 | 555 |
| LAYC PCS | 1 | የህክምና አገዛ፣ የኮምፒዩተር ክህሎት፣ ድርብ ምዝገባ፣ የ GED ዝግጅት፣ እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ፣ የማንበብ እና መፃፍ እውቀት እና የማስላት ችሎታ እድገት | አዋቂ | 149 |
| LEARN DC PCSB | 8 | ቀይጥ ትምህርት፣ የተራዘመ ቀን፣ መላሽ ፍትህ ፕሮግራም | PK3 - 3 | 249 |
| Lee Montessori PCS - Brookland | 5 | Montessori | PK3 - 5 | 286 |
| Lee Montessori PCS - East End | 8 | Montessori | PK3 - 3 | 216 |
| Mary McLeod Bethune PCS | 4, 5 | የጥበብ ውህደት፣ ጥልቅ የቋንቋ ጥናት፣ አለማቀፍ ባካሉሬት | PK3 - 8 | 361 |
| Maya Angelou PCS - ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት | 7 | ቀይጥ እና ግላዊነት የተላበሰ ትምህርት፣ ማህበረሰባዊ ስሜታዊ ትምህርት | አማራጭ | 224 |
| Maya Angelou PCS - YALC | 7 | የአጠቃላይ ትምህርት ልማት (GED) | አዋቂ | 299 |
| Meridian PCS | 1 | በይነዲሲፕሊናዊ ስርዓተ ትምህርት | PK3 - 8 | 621 |
| Monument PCS | 7 | አዳሪ ትምህርት ቤት እና ማጠቃለያ ከአሳዳጊ እንክብካቤ/ ለአደጋ የተጋለጡ ተኮር | አማራጭ | 127 |
| Mundo Verde PCS - Calle Ocho | 5 | ድርብ ቋንቋ/ጥልቅ ትምህርት፣ ትምህርት ለዘላቂነት ትኩረት | PK3 - 4 | 498 |
| Mundo Verde PCS - Cook | 5 | ድርብ ቋንቋ/ጥልቅ ትምህርት፣ ትምህርት ለዘላቂነት ትኩረት | PK3 - 5 | 530 |
| Paul PCS - HS | 4 | አካዳሚክ፣ ጥበባት፣ አትሌቲክስ እና ግሎባል ማበልጸጊያ | 9 - 12 | 438 |
| Paul PCS - MS | 4 | አካዳሚክ፣ ጥበባት፣ አትሌቲክስ እና ግሎባል ማበልጸጊያ | 5 - 8 | 313 |
| Perry Street Prep PCS | 5 | በይነዲሲፕሊናዊ ስርዓተ ትምህርት፤ የተራዘመ የትምህርት ጊዜ | PK3 - 8 | 455 |

## የዲሲ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶች *(የቀጠለ)*

| የትምህርት ቤት ስም | WARD | የፕሮግራም አይነት | 2023 – 24 አገልግሎት ያገኙ የክፍል ደረጃዎች | 2023 - 24 ኦዲት የተደረገ ምዝገባ |
|---|---|---|---|---|
| Richard Wright PCS | 6 | ጋዜጠኝነትና የሚዲያ ስነ ጥበብ | 8 - 12 | 309 |
| Rocketship PCS - Infinity | 5 | የጥበብ ውህደት | PK3 - 5 | 341 |
| Rocketship PCS - Legacy | 7 | ለግል የተበጀ እና ቅይጥ መማር | PK3 - 5 | 609 |
| Rocketship PCS - Rise | 8 | ለግል የተበጀ እና ቅይጥ መማር | PK3 - 5 | 428 |
| Roots PCS | 4 | አፍሪካዊ ተኮር ስርዓተ ትምህርት | PK3 - 5 | 80 |
| SEED PCS | 7 | አዳሪ ትምህርት ቤት | 9 - 12 | 252 |
| Sela PCS | 4 | የድርብ ቋንቋ/ጥልቅ ጥናት | PK3 - 5 | 285 |
| Shining Stars PCS | 5 | Montessori | PK3 - 5 | 215 |
| Social Justice PCS | 5 | የጉዞ ትምህርት፣ የነጻነት ንድፍ አስተሳሰብ፣ እና ሠራተኞች | 5 - 8 | 124 |
| St. Coletta PCS | 7 | ልዩ ትምህርት | አማራጭ | 251 |
| Statesmen PCS | 8 | የአካዳሚክ ክህሎትን የሚያሻሽል ለወንዶች ተስማሚ የሆነ የትምህርት አከባቢ፣ ማህበራዊ ብቃት እና ግለሰባዊ እድገት | 4 - 8 | 307 |
| Children's Guild PCS | 5 | Montessori | አማራጭ | 230 |
| The Family Place PCS | 1 | ESL፣ የህፃናት እድገት ረዳት፣ የስራ ሃይል እድገት፣ ስፓኒሽ፣ የማንበብና የመጻፍ እውቀት፣ 2-Gen አቀራረብ | አዋቂ | 193 |
| Next Step PCS | 1 | የ GED ዝግጅት፣ እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ፣ ድርብ የኮሌጅ ምዝገባ፣ የቀን እና ማታ አማራጮች፣ የመጓጓዣና የህፃናት እንክብካቤ እገዛ | አዋቂ | 510 |
| Sojourner Truth PCS | 5 | ሞንቴሶሪ፣ የተቀናጀ ትምህርት | 6 - 10 | 284 |
| Thurgood Marshall PCS | 8 | የህዝብ ፖሊሲ እና የህግ ትኩረት | 9 - 12 | 338 |
| Two Rivers PCS - 4th Street | 6 | የጉዞ ትምህርት | PK3 - 5 | 390 |
| Two Rivers PCS - Young ES | 5 | የጉዞ ትምህርት | PK3 - 5 | 378 |
| Two Rivers PCS - Young MS | 5 | የጥበብ ውህደት | 6 - 8 | 254 |
| Washington Global PCS | 6 | ዓለም አቀፋዊ ስርዓተ ትምህርት፣ ግለሰብ ተኮር የትምህርት | 6 - 8 | 219 |
| Washington Latin PCS - Anna Cooper MS | 5 | ክላሲካል ትምህርት | 5 - 7 | 258 |
| Washington Latin PCS- MS | 4 | ክላሲካል ትምህርት | 5 - 8 | 393 |
| Washington Latin PCS | 4 | ክላሲካል ትምህርት | 9 - 12 | 356 |
| የዋሽንግተን አመራር አካዳሚ PCS | 5 | ቴክኖሎጂ፣ ኮምፒዩተር ሳይንስ፣ የመሪነት እድገት | 9 - 12 | 398 |
| Yu Ying PCS | 5 | የማንደሪን ቻይንኛ ጥልቅ ቋንቋ ጥናት፤ ዓለምአቀፍ ባካሉሬት | PK3 - 5 | 634 |
| YouthBuild PCS | 1 | እንግሊዝኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ፤ የግንባታ ትምህርት፤ ድርብ ምዝገባ | የአዋቂ ትምህርት | 133 |

# ትምህርት መገምገም

DC PCSB የትምህርት ቤቱን ለተማሪዎቻቸው፣ አስተማሪዎቻቸው እና የትምህርት ቤት ማህበረሰባቸው የሚጠቅሙ ውሳኔዎችን ለማድረግ ያለውን ነፃነት ሳያውክ የዲሲ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤቶችን የትምህርት ቁጥጥር እንዴት በተሻለ ሁኔታ ማጠናከር እና ማሻሻል እንደሚቻል ለመወሰን ከትምህርት ቤት መሪዎች፣ ቤተ ሰቦች፣ ፖሊሲ አውጪዎች፣ የአካባቢ እና የሀገር አቀፍ የትምህርት ኤጀንሲዎች እና ሌሎች አጋሮች ጋር ይተባበራል። ይህ የቦርድ የቁጥጥር ስራ የሁሉንም፣ በተለይም በታሪክ ከተገለሉ ቡድኖች የመጡ የዲሲ ተማሪዎችን ተሞክሮ ያሻሽላል።

የአካዳሚክ ቁጥጥር አካሄዳችን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

## የቻርተር ግምገማዎች እና እድሳት

የትምህርት ቤት ማሻሻያ ድንጋጌ DC PCSB የእያንዳንዱን ትምህርት ቤት ቻርተር ግምገማ ቢያንስ በየአምስት አመቱ አንድ ጊዜ እንዲያካሂድ ያስገድዳል። ቦርዱ እያ ንዳንዱ ትምህርት ቤት የቻርተር ግቦቹን እና የአካዳሚክ ስኬት የሚጠበቁትን ለማሳካት ያለውን ሂደት ይገመግማል። የትምህርት ቤቱ ተገዢነት በሚመለከታቸው የፌ ዴራል እና የአካባቢ ህጎች፣ ቻርተሩን እና የፊስካል አስተዳደርን ማክበር ተገምግሟል።

ከዚህ በታች እንደተዘረዘረው ዘጠኝ የቻርተር ግምገማዎች በ SY 2023 - 24 ተካሂደዋል። [1] በዚህ ጊዜ ምንም የቻርተር እድሳት አልተካሄደም። የቦርድ ድርጊቶችን ዝርዝር በገጽ 31 ላይ ይመልከቱ  ለእያንዳንዱ የድምጽ መስጠት ቀን።

**SY 2023 - 24፦ የ10-አመት ቻርተር ግምገማዎች**

ቦርዱ እነዚህን የ10 ዓመት ግምገማዎች አጽድቋል፦

- የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ዓለም አቀፍ ትምህርት ቤት
- Harmony PCS
- Lee Montessori PCS

**SY 2023 - 24፦ የ20-አመት ቻርተር ግምገማዎች**

ቦርዱ እነዚህን የ25-ዓመት ግምገማዎች አጽድቋል፦

- DC Bilingual PCS
- E.L. Haynes PCS
- Two Rivers PCS

**SY 2023 - 24፦ የ25-ዓመት ቻርተር ግምገማዎች**

ቦርዱ እነዚህን የ25-ዓመት ግምገማዎች አጽድቋል፦

- Meridian PCS
- Perry Street Prep PCS
- Roots PCS

እባክዎን የግምገማ ሪፖርቶችን ለማንበብ https://dcpcsb.org/charter-reviews-and-renewalsን ይጎብኙ።

### ጣልቃገብነቶች እና ጉድለቶችን ማረም

DC PCSB በ SY 2023 - 24 ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ አላወጣም።

[1] የAcademy of Hope PCS የ10-አመት ቻርተር ግምገማ በሴፕቴምበር 2024 ይካሄዳል።

# ጥራት-ተኮር የጣቢያ ግምገማዎች

DC PCSB የትምህርት ቤቶችን አካባቢ እና የትምህርት ጥራትን ለመገምገም የ QSR ተነሳሽነት አዘጋጅቷል። QSR የታሰበው የአጠቃላይ ጥራት ቅጽበታዊ ገጽ እይታን ለማቅረብ እንጂ መምህራንን ለመገምገም አይደለም። DC PCSB ያልተጠበቀ የትምህርት ቤት ጉብኝቶችን ያካሂዳል እና ዘፈ ቀዳዊ ናሙና የመማሪያ ክፍሎችን ይመርጣል። DC PCSB በተለምዶ ተመራጮችን አይመለከትም ነገር ግን ለትምህርት ቤቱ ተልእኮ ወሳኝ ከሆነ የምርጫ ክፍልን ይመለከታል። DC PCSB በክፍል ደረጃዎች ወይም በርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ አጠቃላይ አዝማሚያዎችን ሊያስተውል ቢችልም፣ የQSR ቡድን ጥቆማዎችን አይሰጥም ወይም የተናጠል ምልከታ ውጤቶችን አያጋራም። የQSR ቡድን በLEA ውስጥ ላለው እያንዳንዱ ካምፓስ የጥራት ግምገማ የያዘ የመጨረሻ ሪፖርት ያወጣል።

QSRs የሚከተሉትን ክፍሎች ያቀፈ ነው፦

1. ስለ QSR አጠቃላይ እይታ ለመስጠት ከትምህርት ቤት መሪዎች ጋር ሴክተር-አቀፍ ስልጠና፤
2. የተማሪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ጥበባት (ELA) እና የሂሳብ እና የስራ ናሙናዎች ግምገማ፤
3. የመሠረታዊ ይዘት ክፍሎች እና የልዩ ትምህርት እና ጀማሪ የብዝሃ ቋንቋ ተማሪ ፕሮግራሞች ያልተስተዋሉ ምልከታዎች 75%፤ እና
4. ከትምህርት ቤቱ አመራር ቡድን እና ከ DC PCSB ሰራተኞች ጋር የታቀደ ውይይት።

DC PCSB የQSR ሂደትን በ SY 2023-24 በሚከተሉት ትምህርት ቤቶች አካሂዷል፦

- AppleTree PCS – Columbia Heights
- AppleTree PCS – Douglas Knoll
- AppleTree PCS – Lincoln Park
- AppleTree PCS – Oklahoma Avenue
- AppleTree PCS - Parklands
- AppleTree PCS – Southwest
- Bridges PCS
- Capital City PCS – LS
- Capital City PCS – MS
- Capital City PCS – HS
- Capital Village PCS
- Cedar Tree PCS
- Early Childhood PCS
- Digital Pioneers PCS – Johenning
- Digital Pioneers PCS – Capitol Hill
- Girls Global PCS
- Hope Community PCS - Tolson
- Howard University Middle PCS
- I Dream PCS
- IDEA PCS
- Kingsman PCS
- MM Bethune PCS
- Monument PCS
- Paul PCS – HS
- Paul PCS – MSl
- Social Justice PCS
- Sojourner Truth PCS
- Children’s Guild PCS
- Two Rivers PCS – Young MS
- Washington Global PCS
- YouthBuild PCS

https://dcpcsb.org/qualitative-site-reviews ላይ ስለ QSR ተነሳሽነት የበለጠ ይወቁ።

# የትምህርት ቤት እቅድ ማውጣት

እንደ ዋሽንግተን ዲሲ ገለልተኛ የቻርተር ትምህርት ቤት ፈቃጅ DC PCSB አዲስ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ለመመስረት ከሚፈልጉ ቡድኖች እና አሁን ካሉት የትምህርት ቤት ቡድኖች የሚያገለግሉትን ክፍሎች ወይም እድሜዎች ለማስፋፋት፣ ለማዛወር እና ዳግም ለማዋቀር የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ይገመግማል። እንዲሁም፣ DC PCSB ከሻረ፣ ቻርተርን ካላሳደሰ፣ ወይም ትምህርት ቤት ቻርተሩን በፈቃዱ ከተወ ትምህርት ቤቶች ሊዘጉ ይችላሉ። በዚህ የትምህርት አመት የጸደቁትን የቻርተር ማሻሻያዎች ዝርዝር፣ ከSY 2024 – 25 ጀምሮ የሚከፈቱ አዳዲስ ካምፓሶችን እና መገልገያዎችን ጨምሮ፣ ገጽ 31ን ይመልከቱ።[2] አዲሱ የትምህርት ቤት መክፈቻዎች፣ በ SY 2023-24 ተፈጻሚ የሚሆኑ የክፍል ጭማሪዎች፣ ዳግም ማዋቀር እና ማዛወሪያዎች ከዚህ በታች ናቸው።

### አዲስ የትምህርት ቤት ቻርተር ማመልከቻዎች

በሴፕቴምበር 27፣ 2023፣ DC PCSB የ2024 ቻርተር ማመልከቻ መመሪያዎችን አውጥቷል። አዲሱን የትምህርት ቤት ማመልከቻዎቻቸውን እና የDC PCSB እንዴት እንደሚገመግማቸው የሂደቱን መስራች ቡድኖች መከተል እንዳለባቸው ያብራራሉ። የ2024 ቻርተር ማመልከቻ መመሪያዎች እና ሁሉም ተዛማጅ ግብአቶች https://dcpcsb.org/start-charter-school ላይ ይገኛሉ።

በማርች 8፣ 2024፣ DC PCSB አዲስ የህዝብ ቻርተር ትምህርት ቤት ለማቋቋም አንድ ማመልከቻ ተቀብሏል። Oxford Preparatory PCS በዋርድ 7 የK - 8 ቅይጥ ትምህርት ፕሮግራም ለመክፈት ሐሳብ አቅርቧል። መስራች ቡድኑ ማመልከቻውን በማርች 18፣ 2024 ከግንዛቤ ከመግባት ሰርዟል፣ በዚህም የቻርተር ማመልከቻ ግምገማ ዑደቱን አጠናቋል።

### አዲስ የትምህርት ቤት መክፈቻዎች

በ SY 2023 - 24 ምንም አዲስ LEAs ወይም ካምፓሶች ሥራ አልጀመሩም። ሆኖም፣ በ SY 2024 - 25 ሁለት አዳዲስ ካምፖሶች ይከፈታሉ። የትምህርት ቤት እቅድ ዝግጅት ገፅን https://dcpcsb.org/school-planning ላይ ይጎብኙ

### የትምህርት ቤት መዝጊያዎች

በ SY 2023-24 መጨረሻ ምንም LEAs ወይም ካምፓሶች አልተዘጉም።

